UW Medicine
VALLEY MEDICAL CENTER

**የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች መምሪያ**

## የ VMC ክፍያ መጠየቂያና መሰብሰቢያ መመሪያ

| | |
|---|---|
| **መምሪያ፡-** | **የታካሚ የፋይናንስ አገልግሎቶች መምሪያ - የደንበኛ አገልግሎት ክፍል** |
| **የመመሪያው አርዕስት፡-** | **የፋይናንስ ድጋፍ** |
| **የመመሪያ ቁጥር፡-** | **PFS.5000.1** |
| **ዓላማ፡-** | **የሥራ አፈጻጸም መመሪያው በታካሚ መከፈል ያላባቸውን ቀሪ ሒሳቦች ለማስከፈል በሚገባ የተገለጸ፣ በኢንዱስትሪው የጥራት ደረጃ ፕሮቶኮል መሠረት የተዘጋጀ ደንብን በግልጽ ያስቀምጣል። የሥራ አፈጻጸም መመሪያው ከታካሚ መሰብሰብ ካለባቸው ሒሳቦች እና የውጭ የክፍያ ሰብሳቢ ወኪል ድርጅት ሒሳቦች ጋር የተገናኙ የሒሳብ መላኪያዎች ጋ የተገናኙ ወጥነት ያላቸው የአሠራር ሂደቶችን እና የኦዲት አደራረግ እንቅስቃሴዎችን አፈጻጸም ሂደት ያስቀምጣል።**<br><br>**የቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) በታካሚው በግሉ (ወይም ክፍያውን መፈጸም ባለበት ወገን) መከፈል ያለባቸውን ቀሪ ሒሳቦች ለማስከፈል የሚቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል። ሆስፒታሉ በራሱ ያልተከፈለውን ክፍያ በሙሉ ለማስከፈል የተቻለውን ጥረት ካደረገ በኋላ ሳይከፈሉ ለቀሩ ሒሳቦች ለሰጠው የሕክምና አገልግሎት የክፍያ ማስከፈል ተጨማሪ እርምጃዎችን እንዲወስዱለት ወደ ሦስተኛ ወገን (የውጭ) ፕሮፌሽናል የሒሳብ አጣሪ (ሰብሳቢ) ድርጅቶች ጉዳዩን የሚያስተላልፍ ይሆናል።** |

**አፈጻጸም ሥነ ሥርዓት፡-**

***<u>አጠቃላይ የራስ በራስ ክፍያ መፈጸሚያ መርሐ ግብር</u>***

| | |
|---|---|
| የመጀመሪያ ሒሳብ መግለጫ | ቀን 1 |
| ሁለተኛ የሒሳብ መግለጫ | ቀን 31 |
| ሦስተኛ የሒሳብ መግለጫ | ቀን 61 |
| የመጨረሻ ማስታወቂያ | ቀን 91 |
| መጥፎ ብድር (ዕዳ) ማወራረጃ | ቀን 120 |

***<u>አጠቃላይ የቢዝነስመርሆዎች፡-</u>***

1. ቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) የጤና መድን የሌላቸውን ወይም ውስን የጤና መድን ሽፋን ያላቸውን ታካሚዎች የሚያጋጥማቸውን በጉልህ የሚታይ ገንዘብ ነክ ችግር ወይም ጫና ከግምት ውስጥ ያስገባል። የመድን ሽፋን ለሌላቸው ታካሚዎች በእኛ የሥራ ተቋራጭነት ውል ካላቸው የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅቶች በኩል የሚሰጠውን የዋጋ ቅናሽ ያክል ተመጣጣኝ የሆነ የዋጋ ቅናሽ እንሰጣለን።

2. የመድን ሽፋን የሌላቸው ታካሚዎች ለሚቀርባቸው ያልተከፈለ ሒሳብ(ቦች) ወዲያውኑ እንደከፈሉ ተፈጻሚ የሚሆኑ የዋጋ ቅናሽ አማራጮችን ያገኛሉ። (እባክዎ የመድን ሽፋን የሌላቸው እና በፍጥነት በመክፈል የሚገኝ የዋጋ ቅናሽ መመሪያ የሚለውን ሰነድ ይመልከቱ)።

3. በአንድ ጊዜ ቀሪውን ሒሳብ ሙሉ በሙሉ ለመክፈል እንደሚቸገሩ ለሚገልጹ ታካሚዎች ወይም ክፍያ የመፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች ያለ ምንም ወለድ ለ12 ወራት ተቆራርጦ የሚከፈል የተራዘመ የክፍያ አፈጻጸም አማራጭ ይሰጣቸዋል። በሁሉም የሆስፒታሉ ያልተከፈሉ ሒሳቦች ላይ ዝቅተኛው መክፈል የሚቻለው ሒሳብ የዋጋ መጠኑ $50 ሲሆን ለሐኪም መክፈል ያለበት ክፍያ ዝቅተኛው ተመን $25 ነው፤ ክፍያውም ከ12 ወራት በላይ መሆን የለበትም። ታካሚው ወይም ሒሳብ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ወገን ክፍያውን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ለመጨረስ የተሰጠውን የ12 ወራት ጊዜ በአግባቡ መጠቀም የማይችል ከሆነ፣ ከዚህም ለተራዘመ የክፍያ ማስተካከያዎች የባንክ ፋይናንሲንግ ሊቀርብለት ይችላል።

4. የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) በአጋር ባንክ አማካይነት የረዥም ጊዜ የክፍያ እቅድ አማራጮችን ያቀርባል።

5. በውስን ገቢ ምክንያት ታካሚው ክፍያውን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ከፍሎ ማጠናቀቅ እንደማይችል ከገለጸ፣ ታካሚው ወይም ክፍያውን የሚፈጽምለት ወገን የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት የቀሪ ሒሳብ አከፋፈል ሥርዓት ማሻሻያ ስለማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥለት አግባብነት ያላቸውን ደጋፊ የሒሳብ ሰነዶች ዓባሪ በማያያዝ የፋይናንስ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ እንዲሞላ የተዘጋጀው ቅጽ ይሰጠዋል። (እባክዎ የፋይናንስ ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያውን ያንብቡ)።

6. የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ብቁ ለሆኑ የኪንግ ካውንቲ የህዝብ ሆስፒታል ዲስትሪክት #1 የቤት ባለቤቶች ለንብረት ታክስ ክፍያ የቫሊ ታክስ ክፍፍል ማሻሻያ ያቅርብላቸዋል። ሁሉም የሦስተኛ ወገንና የኢንሹራንስ ክፍያዎች ከተከፈሉ በኋላ የቫሊ ክፍፍል እዳ ለቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ከኪስ መክፈል ባለባቸው ወጪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

   ማስተካከያው ገንዘብ መጠን ለሆስፒታል ዲስትሪክት ቁጥር #1 በይፋዊው የኪንግ ካውንቲ የታክስ መዝገቦች መሠረት በተከፈሉ ግብሮች ላይ በመመርኮዝ የሚወሰን ይሆናል። ለማናቸውም የሆስፒታሉ ዲስትሪክት #1 ነዋሪ የሚደረገው የቫሊ ታክስ ክፍፍል ማስተከከያ የዕድሜ ልክ ከፍተኛው የገንዘብ መጠን $3,000 ነው።

7. በቼክ / በክሬዲት / በዴቢት ካርድ ክፍያ ፈጽመው በቂ የሆነ ፈንድ በሒሳባቸው ላይ ባለመኖሩ ተመላሽ የሆነባቸው ታካሚዎች ወይም ክፍያ የመፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖች በሒሳባቸው ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ተጨማሪ የ NSF ክፍያ ይሰጣቸዋል። አሁን ላይ የቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ለማናቸውም በቂ ስንቅ ስለሌላቸው ተመላሽ የሆኑ የቼክ ወይም የክሬዲት / ዴቢት ካርድ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች $35.00 የተመላሽ ቼክ ክፍያን ያስከፍላል።

8. ቫሊይ የህክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ከመጀመሪያ መግለጫው በኋላ ባሉ 30 ቀናት እና ከዚያ በኋላ በየወሩ የግል-ከፋይ መግለጫ ባላቸው የሂሳብ ቁጥሮች ላይ 1% የወለድ ተመን ያስከፍላል። በክፍያ ዕቅዶች ላይ ያሉ፣ ወይም ግምገማ ላይ ያሉ ወይም እየተጠባበቁ ያሉ መለያዎች ወደ የግል-ከፋይ ኡደት እስከሚመለሱ ድረስ ወለድ አይከፍሉም።

9. ቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) በክፍያ ማስከፈሉ ሂደት ወቅት ለታካሚው የላከው ደብዳቤ ተመላሽ ከሆነበት፣ ትክክለኛው አድራሻን ማግኘት የሚቻል እንደሆነ ለማወቅ ሲባል አግባብነት ያላቸው ክትትል ማድረጊያ ዘዴዎችን በመጠቀም የባንክ ሒሳቦች ላይ ማጣራት ይደረጋል። አዲስ እና ትክክለኛ መረጃ ከተገኘ፣ ሒሳቡ በዚህ መሠረት ይስተካከል እና የክፍያ ማስፈጸሙ ሂደት ካቆመበት እንዲቀጥል ይደረጋል። ወቅታዊ አድራሻን ማግኘት ካልተቻለ፣ ሒሳቡ በሒሳቡ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ አግባብነት ያለው እርምጃ እንዲወሰድ ሒሳቡ ይገመገማል ወይም ተጨማሪ ክፍያን የማስከፈል ጥረቶች እንዲደረጉ ወደ ክፍያ ሰብሳቢ ድርጅት ሒሳቡ እንዲተላለፍ ይደረጋል።

10. የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) የራስ-በራስ የክፍያ ማስፈጸሚ ጥረቶች በዋሽንግተን ስቴት እና Medicare / Medicaid ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት የሚከናወን ይሆናል።

11. <u>የሕክምና ወጪ እዳዎች፡-</u>

አንድ ታካሚ በአደጋ ወይም በሌላ ሕገወጥ ተግባር ምክንያት ጉዳት ሲደርስበት፣ ለደረሰበት ጉዳት ተጠያቂው ሌላ ወገን መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የጤና መድን ኢንሹራንስ ኩባንያቸው አጠቃላይ የሕክምና አገልግሎቶች ወጪውን አይሸፍንም። ከዚህ በተጨማሪ፣ አንድ ታካሚ የመድን ኢንሹራንስ ላይኖረው እና ለጉዳቱ ተጠያቂ ከሆነው ወገን ወጪው እንዲሸፈንለት ለማድረግ ሊፈልግ ይችል ይሆናል። ይህ በሚያጋጥምበት ወቅት፣ UW/Valley Medical Center ወደፊት ለሚፈጸመው ክፍያ የሕክምና ወጪ ማስከፈያ ትስስር ማስጀመሪያ ፋይል ሊከፍት ይችላል። ትስስር ሲባል በአንድ የሪል እስቴት ወይም የግል መኖሪያ ቤት መያዣነት ዕዳ ክፍያን በተመለከተ ዋስትና የሚያዝበት የዋስትና መጠበቂያ መንገድ ነው።

12. <u>ክፍያ እንዲፈጸም በዕዳ የተያዙ ሒሳቦች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-</u>

- ክሬዲት ሪፖርት ከመጀመሪያው ድህረ ክፍያ መጠየቂያ 180 ቀናት በኋላ ይደረጋል።
- ከመጀመሪያው ድህረክፍያ በኋላ እስካሉት 240 ቀናት ድረስ ባልተከፈሉ ውዝፍ ዕዳዎች በፍርድ ቤት ክስ ላይመሠረት ይችላል።
- የስልክ ጥሪ
- አግባብነት ካላቸው ተከታይ ከደመዎዝ ላይ ተቆራጭ ማስደረግ ጋር ሕጋዊ እርምጃዎች
- የሕክምና ወጪ ትስስሮች
- ቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center ) በማናቸውም ሒሳብ ላይ ለሚወሰድ ሕጋዊ እርምጃ ሥልጣን መስጠት ይኖርበታል።
- የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) እዚህ ግባ የሚባል የሥራ ቅጥር ከሌለ በሕግ ተጠያቂነትን ላይፈቅድ ይችል ይሆናል።
- ያልተከፈሉ ሒሳቦች ለአንድ ዓመት በወኪል ድርጅት ተከፋይ እንዲደረጉ ይጠበቃሉ፣ የአከፋፈል ስምምነት ካልተደረሰ ወይም ሕጋዊ የፍርድ ቤት ውሳኔ ካልተሰጠ በቀር ከዚህ በኋላ ሌላ ወኪል ድርጅት ጉዳዩን እንዲይዘው ይደረጋል።
- ለሁለተኛ ክፍያ ሰብሳቢ ድርጅት ጉዳዩ ከተላለፈ በኋላ ከአንድ ተጨማሪ ዓመት ቆይታ በኋላ በ90 ቀናት ቀደም ብሎ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ካልታየ ተመላሽ ይሆናሉ።
- ከሁለተኛ ምደባ በኋላ ባለመከፈላቸው ተመላሽ የሆኑ ሒሳቦች በወኪል ድርጅት በኩል ሊሰበሰቡ ያልቻሉ በሚል ተስተካክለው ሊሰበሰቡ እንዳልቻሉ ሒሳቦች ይቆጠራሉ።
- ያልተከፈሉ ቀሪ ሒሳቦች፣ ለሰባት ዓመታት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ለዐሥር ዓመታት በዋስትና ሰጪው ወገን የብድር ታሪክ ማሳያ ሰነድ ላይ ይቆያል።

## *የጤና እንክብካቤ መድን ሽፋን የሌላቸው ታካሚዎች*

1. የጤና እንክብካቤ መድን ሽፋን የሌላቸው የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ታካሚዎች ከሆስፒታሉ ከተሰናበቱ በግምት ከ 5 ቀናት በኋላ ለተሰጣቸው የሕክምና አገልግሎት ወጪዎች አጠቃላይ የሒሳብ መግለጫ ይላክላቸዋል። ስለሚኖራቸው የፋይናንስ አማራጮች ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት እንዲችሉ ከደንበኛ አገልግሎት መምሪያ አድራሻ ጋ መረጃ ሰጪ ሰነድ አብሮ ይላክላቸዋል።

   **ማሳሰቢያ፦** የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ወደ ሆስፒታሉ የገቡ የጤና እንክብካቤ የመድን ሽፋን ለሌላቸው ታካሚዎች የ Medicaid ማመልከቻ እንዲያስገቡ እገዛ ያደርግላቸዋል። ታካሚዎች ለ Medicaid ብቁ መሆናቸውን ለመወሰን ጉዳያቸው የሚታይ ሲሆን አግባብነት ያለው ሆኖ ከተገኘ ማመልከቻ በማስገባቱ ሂደት ላይ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

2. ታካሚዎች መክፈል ካለባቸው ክፍያ 30% ዋጋ ቅናሽ በ *የመድን ሽፋን ለሌላቸው የሚሰጥ የዋጋ ቅናሽ* ያገኛሉ።

3. ቫሊ ለታካሚው ወይም ክፍያውን የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ወገን 4 የሒሳብ መግለጫ ማስታወቂያዎችን በመላክ ስለ ቀሪው ያልተከፈለ ሒሳብ ያሳውቃቸዋል። የክፍያ አማራጮችን መሰረት በማድረግ፣ ከመጀመሪያው የመግለጫ ቀን በኋላ ካሉት 14 ቀናት ጀምሮ ታካሚዎች የስልክ ጥሪዎች፣ የጽሁፍ መልዕክቶች፣ ወይም የ MyChart ማሳወቂያዎች ሊደርሷቸው ይችላሉ።

4. ክፍያው ሙሉ በሙሉ ካልተከፈለ ወይም የአከፋፈል ስምምነት ላይ ካልተደረሰ፣ የመጨረሻ ቅድመ ክፍያ ማስታወቂያ ክፍያውን የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ወገን የሚላክለት ሲሆን በዚህ ማስታወቂያ ላይ ቀሪው ሒሳብ የሒሳብ መግለጫው በተላከ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ካልተከፈለ ወይም የአከፋፈል ስምምነት ካልተደረሰ ሒሳቡን ተጨማሪ የክፍያ ማስከፈል እርምጃዎች በመጠቀም ከማስከፈል ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለን የሚያስታውቅ ይሆናል።

5. ክፍያው ሙሉ በሙሉ ካልተፈጸመ፣ ሌላ የአከፋፈል ስምምነቶች ካልተደረጉ፣ ሒሳቡ የተቀመጠለትን የ120 ቀን የሒሳብ ዑደት ገደብ ከጨረሰ፣ እና ሁሉም መስፈርቶች ከተሟሉ፣ ሒሳቡ በፕሮፌሽናል ያልተከፈለ ሒሳብ ሰብሳቢ ድርጅት እንዲያዝ ይደረጋል።

## የጤና እንክብካቤ መድን ሽፋን ያላቸው ታካሚዎች

1. የቫሊ ሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ሁሉንም የታወቁ የመድን ሽፋን ሰጪ ድርጅቶች ክፍያ እንዲከፍሉት ጥያቄውን ያቀርባል። ታካሚው ማናቸውንም ቀሪ ሒሳቡን እንዲከፍል ከመጠየቁ በፊት በቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) እና በከፋዩ መሀል ቀድሞ የተፈጸመ የመድን ውል ያለ ከሆነ የቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ከመጀመሪያው ከፋይ እና ሁለተኛው ክፍያ እስከሚፈጸምለት ድረስ ይጠብቃል።

2. ቫሊ የሕክምና ማዕከል (Valley Medical Center) ከኢንሹራንስ ኩባንያ(ዎች) ምላሽ ካገኘ በኋላ ለታካሚው ቀሪ ሒሳቦች መግለጫ የሒሳብ ሰነድን ያዘጋጃል። ሁሉም እንዲከፈሉ የሚጠበቁ ክፍያ (ክፍያዎች) ከተከፈሉ በኋላ፣ ቫሊ ለታካሚው ወይም ክፍያውን የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ወገን 4 የሒሳብ መግለጫ ማስታወቂያዎችን በመላክ ስለ ቀሪው ያልተከፈለ ሒሳብ ያሳውቃቸዋል። የክፍያ አማራጮችን መሰረት በማድረግ፣ ከመጀመሪያው የመግለጫ ቀን በኋላ ካሉት 14 ቀናት ጀምሮ ታካሚዎች የስልክ ጥሪዎች፣ የጽሁፍ መልዕክቶች፣ ወይም የ MyChart ማሳወቂያዎች ሊደርሷቸው ይችላሉ።

3. ክፍያው ሙሉ በሙሉ ካልተከፈለ ወይም የአከፋፈል ስምምነት ላይ ካልተደረሰ፣ የመጨረሻ ቅድመ ክፍያ ማስታወቂያ ክፍያውን የመክፈል ኃላፊነት ላለበት ወገን የሚላክለት ሲሆን በዚህ ማስታወቂያ ላይ ቀሪው ሒሳብ የሒሳብ መግለጫው በተላከ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ካልተከፈለ ወይም የአከፋፈል ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ሒሳቡን ተጨማሪ የክፍያ ማስከፈል እርምጃዎች በመጠቀም ከማስከፈል ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለን የሚያስታውቅ ይሆናል።

4. ክፍያው ሙሉ በሙሉ ካልተፈጸመ ወይም ሌሎች የአከፋፈል ስምምነቶች ካልተደረጉ፣ ሒሳቡ የተቀመጠለትን የ120 ቀን የሒሳብ ዑደት ገደብ ከጨረሰ፣ እና ሁሉም መስፈርቶች ከተሟሉ፣ ሒሳቡ ሆስፒታሉ በሚቀጥረው በፕሮፌሽናል ያልተከፈለ ሒሳብ ሰብሳቢ ድርጅት እንዲያዝ ይደረጋል።